
ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

# የአሥራ ሦስቱ ኤጲስ ቆጶሳት

## የምርጫ አፈጻጸምና

# አጭር የሕይወት ታሪክ



ጥር ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ም ።

ከሕትመትና የሕይወት ታሪክ አዘጋጅ ኰሚቴ የቀረበ ።

# መ ግ ቢ ያ

በ፲፱፻፷፮ ዓ/ም በየካቲት ወር በሀገራችን የተደረገው ከፍተኛ የፖለቲካ ለውጥ ፀኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም የተሐድሶ ጎዳና እንድትከተል በማድረጉ እስከአሁን በቤተክርስቲያን የተደረገው ለውጥ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ።

በመጀመሪያ ደረጃ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ምእመናንና ካህናት ቤተ ክርስቲያኒቷን ለመ ምራት ይችላሉ ብሎ ያመነባቸውን አንድ አባት መርጦ ፓትርያርክ አድርጐ በመሾም ለመጨረሻው ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን ስልጣንና ማዕረግ አብቅቷቸዋል ።

ከዚህ በተገኘው ልምድ አሁን ደግሞ መላው ሕዝበ ክርስቲያንና የቤተ ክርስ ቲያን አገልጋዮች ካህናት ቤተ ክርስቲያንን ያሻሽላሉ ፤ ምእመናንንም ይመራሉ ብለው ያመኑባቸውን አሥራ ሦስት ምሁራን ከያሉበት ቦታ ፈልገው ለኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ መርጠው እንዲሾሙ አድርገዋል ።


እውነትም የተመረጡት ኤጲስ ቆጶሳት የዛሬዎቱን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለመምራት እንደሚችሉ ከያንዳንዳቸው የህይወት ታሪክ ለመረዳት ይቻላል ።

አዲሶቹ ኤጲስ ቆጶሳት ቤተ ክርስቲያንን በተሐድሶ ጎዳና ለመምራት በሚያ ደርጉት ጥረት ሁሉ የመረጧቸው መላ የኢትዮጵያምእመናንናካህናት እንደሚከተሏቸው አይጠረጠርም ።

# አዲስ የተመረጡት ኤጲስ ቆጶሳት የምርጫ አፈጻም ሁኔታ


የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለምትጠብቀው የተሟላ አገልግሎት አዳዲስ ኤጲስ ቆጶሳት እንዲመረጡ ቅዱስ ሲኖዶሱ በወሰነው መሠረት ጥር ፩ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ/ም በመንበረ ፓትርያርኩ ከመንግሥት የተወከሉ ተመልካቾች በተገኙበት የኤጲስ ቆጶሳቱ ምርጫ ስነ ሥርዓት ተካሂዷል ።

ከ፲፬ ክፍላተ ሀገርና ከአዲስ አበባ ጭምር በካህናትና በምእመናን የተወከሉ መራጮች ተሳታፊ በሆኑበት በዚህ የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ ከቀረቡት ፳፩ ቆሞሳት ፲፪ በድምፅ ብልጫ በኤጲስ ቆጶስነት ተመርጠዋል ፥
በድምፅ ብልጫ ያለፉት ፲፪ ቆሞሳትም



፩ኛ/ አባ መዓዛ ቅዱሳን ገብረ ሕይወት
፪ኛ/ » መዝገበ ሥላሴ ክፍሌ
፫ኛ/ » ዜና ገብርኤል በኀ ሰው
፬ኛ/ » ዘሊባኖስ ፈንታ
፭ኛ/ » ያሬድ ግርማዬ
፮ኛ/ » ተክለ ማርያም አሥራት
፯ኛ/ » ፍስሐ ጽዮን ጌታሁን
፰ኛ/ » ገብረ ሚካኤል መንገሻ
፱ኛ/ » ስብሐት ለአብ በየነ
፲ኛ/ » ሐዋዝ ብርሃኑ
፲፩ኛ/ » ኀሩይ ወልደ ሰንበት
፲፪ኛ/ ፀጋዬ ቢሆነኝ

ሲሆኑበተጨማሪም አባ ላዕከ ማርያም ማንደፍሮ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያ በሰሜን አሜሪካ ኦርቶዶክሳውያን ምዕመናን በከፍተኛ ድምፅ የተመረጡ ስለሆነ ከነዚህ አዲስ ከሚሾሙት ኤጲስ ቆጶሳት ጋር ሢመተ ጵጵስና ተቀብለው ወደመረጣቸው ሕዝብ ለአገልግሎት የሚላኩ መሆናቸው ታውቋል ።



መራጮች ከአስመራጭ ኮሚቴ የምርጫ ካርድ ሲረከቡ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ጊዜ ይህን ያህል ኤጲስ ቆሞሳት ስታ ስመርጥ በቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ ከፍተኛውና የመጀመሪያው ነው ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ድኅነትንና በሽታን ፣ ብዝበዛንና ጭቆናን ለማስወገድ የለውጥ ትግል በምታደርግበት በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትጋትና ጥረት ባለው መንፈሳዊ አመራር ካህናትንና ምእመናንን በሰበካ ጉባኤ በማደራጀትና የራስዋን ችግር በራስዋ በማስወገድ የበኩሏን ድርሻ በሰፊው ማበርከት ስላለበት የእነዚህ ኤጲስ ቆጶሳት መመረጥ ለዚህ ዓላማና ተግባር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ቅዱስ ሲኖዶ ሱና መላው ሕዝበ ክርስቲያን ተስፋ ጥሎበታል ።

የአዳዲስ ኤጲስ ቆጶሳቱ የምርጫ ሥነ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ከጥር ፳ ቀን እስከ ጥር ፴ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም ድረስ ተመራጮቹ ቆሞሳት ስለ ኤጲስ ቆጶሳት ኃላፊነትና ተል እኮ ፣ ስለ ስብከተ ወንጌል መስፋፋት ፣ ስለ ሰበካ ጉባኤ መጠናከር ፤ ቤተ ክርስቲያን ለወጣቶች ማድረግ ስለ አለባት መልካም አቀባበልና ስለ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት ስለሌላውም የቤተ ክርስቲያኒቱ የአስተዳደር ይዘት ብፁዕ ወቅዱስ የኢትዮ ጵያ ፓትርያርክ ፣ የቅዱስ ሲኖዶስ ዓባሎችና የአስመራጭ ኮሚቴ ዓባላት እንዲሁም የቤተ ክህነት ተ/ዋና ሥራ አስኪያጅ በተገኙበት ፲ ቀን የፈጀው ይይትና ጉባኤ አድርገዋል።



የኢ.ኤ.ስ ቆጳሳት ምርጫ በመካሄድ ላይ እንዳለ ።

# አባ መዓዛ ቅዱሳን ገብረ ሕይወት

አባ መዓዛ ቅዱሳን (ገብረሕይወት) በትግራይ ክ/ሀገር በሁለት አውላሎ አውራጃ ዐፁዳ ቅ/ጊዮርጊስ ቀበሌ ከአባታቸው ከአቶ ገ/ሕይወት ጸዕዱና ከእናታቸው ከወይዘሮ ወለተክርስቶስ ግብረቱ በ፲፱፻፳፫ ዓ/ም ግንቦት ፲፪ቀን ተወለዱ ።

በተወለዱበት አካባቢ ድርባ አቡነ ያሳይ በሚባል ቦታ የኔታ ወ/ ገብርኤል ከሚ ባሉ መንፈሳዊ አባት መሠረተትምህርት ተማሩ ። ከዚያም ወደ ጐንደር ሄደው የኔታ ኃይሉ ከሚባሉ ፣ መምህር ፀዋትወ ዜማ ተማሩ።ቀጥሎም በዚያው ክ/ሀገር በሰሜን አውራጃ ደረስጌ በሚባል ደብር ከየኔታ መንበሩ የቅኔ ትምህርት ተማሩ ። በዚሁ ወቅት ከብፁዕ አቡነ ይስሐቅ የዲቁና ማዕርግ ተቀበሉ ።



አባ መዓዛ ቅዱሳን ገብረ ሕይወት

ከዚያ በኋላ አንዳቤት ወረዳ በሻሜ ጊዮርጊስ ደብር ከመምህር ጥበቡ ቅኔ ተማሩ ከዚያም ከመምህር ጌጡ ተሰማ ቅኔና መጻሕፍተ ብሉያት እንዲሁም አቡሻሕር (የቁጥር ትምህርት) ተማሩ ። ከዚህ በኋላ በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም ወደአዲስ አበባ መጥተው በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት ከመጋቤ ሐዲስ ወ/ሚካኤልና ከመምህር ገ/ማርያም ዓለሙ የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ ተምረው በመምሕርነት ተመርቀዋል ። እንዲሁም ከመምህር ገ/ሕይወት ሠይፉ የፍትሐ ነገሥት ትምህርት ከተማሩ ፣ በኋላ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ት/ቤት ገብተው የማስተማርና የስብከት ዘዴ ትምህርት አጥንተው ተመርቀዋል ።

ከዚህ በኋላ የሃይማኖት ና የመጽሐፍ ቅዱስ መምሕር በመሆን ዱር ተፈሪ መኰንን ተብሎ ይጠራ በነበረው ት/ቤት ለ፭ዓመት ያህል ካስተማሩ በኋላ በ፲፱፻፶፰ ዓ/ም ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ በቲዎሎጂ ትምህርት በዲፕሎማ ተመርቀዋል ።

ወ ደ ሀ ገ ራ ቸው ተመልሰው ከ፶፰ እስከ ፲፱፻፷ ዓ/ም ድረስ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ም/አስተዳዳሪ በመሆን አገልግለዋል ። እንዲሁም በሐዋርያዊ ድርጅት የሬዲዮ ፕሮግራም አዘጋጅ በመሆን የመጽሐፍ ቅ ዱ ስ ት ም ህ ር ት ለብዙ ጊዜ አስተምረዋል ከዚህ በኋላ በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም ለከፍተኛ ትምህርት ወደእንግሊዝ ሀገር ሄደው የፍልስፍና ትምህርት ለ፫ዓመት ያህል በመማር በባችለር ዲግሪ ተመርቀዋል ።
በአገልግሎትም ረገድ አ ባ መዓዛ ቅ ዱ ሳ ን ከ፲፱፻፶፱ ዓ/ም ጀ ም ሮ የ ተ ም ሮ ማስተማርን ማኅበር ከመሠረቱት አንዱ ከመሆናቸውም በላይ ዛሬም ቢሆን በየሳምንቱ እሁድና ቅዳሜ ባለማቋረጥ ተልዕኮአቸውን ይፈጽማሉ ።

አባ መዓዛ ቅዱሳን ከ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ጀምሮ እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ድረስ ቀደም ሲል በምክትልነት በኋላም በዋና አስተዳዳሪነት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሰፊ አገልግሎት አበርክተዋል ።

አባ መዓዛ ቅዱሳን በአሁኑ ጊዜ ከ፲፱፻፷፰ እስከ ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በባህልና እስፖርት ሚኒስቴር መርሐ ልሳን በሚባለው ክፍል ተመድበው ሠርተዋል ።

አባ መዓዛ ቅዱሳን የምንኩስና ማዕርግ የተቀበሉት በ፲፱፻፶፫ ዓ/ም በነሐሴ ወር ማለት ነሐሴ ፯ ቀን በደብረሊባኖስ ገዳም ሲሆን ከማዕርገ ቅስና እስከ ማዕርገ ምንኩስናና ቁምስና ድረስ ያለውን ማዕርግ የተቀበሉት ከብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ነው ።

## አባ መዝገበ ሥላሴ ክፍሌ

አባ መዝገ ሥላሴ ክፍሌ በወሎ ክፍለ ሀገር በ፲፱፻፴፪ ዓ/ም ተወለዱ ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በቤተ ክርስቲያን ልማድ መሠረተ ትምህርት ማለት ፊደል ንባብና ዳዊት እንዲሁም የቃልትምህርት ከአጠናቀቁበኋላ ወደ ላስታ በመሄድ ዜማዝምዕራፍና ጾመ ድጓ ከመሪጌታ አብተው ዘንድ በግዳን ወረዳ በደርጌ ገብርኤል ተምረዋል ። ከዚህ በኋላ በላስታ አውራጃ ከመምህር ክፍለ ማርያምና በሸዋ ክፍለ ሀገር በአዲስ ዓለም ከመምህር አፈወርቅ የቅኔ ትምህርት ተምረዋል ።

ቀጥሎም ትምህርታቸውን በማስፋፋት ትርጓሜ ሐዲስ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ከመምህር ፍሥሓ ክርስቶስ ፤ ከመምህር ገብረ ሕይወት ደብረ ጽጌ ገዳም ፤ ሃይማኖተ አበው ከመምህር ቢረሳው በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተምረዋል በተጨማሪ የቅዳሴ ዜማ በደብረ ጽጌ ገዳም ከመምህር ልዑል አጥንተዋል ።

አባ መዝገበ ሥላሴ ክፍሌ ከዚህ በኋላ ወደ ሐረር ክፍለ ሀገር በመሄድ በልዑል ራስ መኰንን መምህራን ማሠልጠኛ መንፈሳዊ ት/ ቤት ገብተው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ከፍተኛ የመንፈሳዊ ትምህርት ለመከታተል ወደ ውጭ ሀገር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተላኩ በመጀመሪያ ትምህርታቸውን የተከታተሉት በግሪክ ሀገር በደሴተ ፍጥም በሚገኘው የቲኦሎጂ ሴሚናሪ ለሁለት ዓመታት ያህል ተምረው በዲፕሎማ ተመረቁ ፤ ቀጥለውም በአቴን ዩኒቨርሲቲ የቲኦሎጂ ትምህርት ለአራት ዓመታት ያህል ከተማሩ በኋላ በባችለር የቲኦሎጂ ዲግሪ ተመርቀዋል ።





አባ መዝገበ ሥላሴ ክፍሌ


አባ መዝገበ ቋንቋ መማር ፍላጎት ያላቸው በመሆኑ ፣ በግሪክ ሀገር ይከታተሉ የነበሩትን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ለፈረንሣይኛ ቋንቋ ትምህርት ወደ ሲዊትዘርላንድ ሄዱ ። በሲዊትዘርላንድ ውስጥ በሚገኘው ፍሪቡርግ ዩኒቨርሲቲ በሚባለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ የአንድ ዓመት የፈረንሣይኛ ትምህርት ተምረው ሰርትፊኬት አግኝተዋል እንዲሁም እስከ ቅርብ ጊዜ በነበሩበት በኢየሩሳሌም ውስጥ በደብረ ጽዮን በሚገኘው የግሪኮች የቲኦሎጂ ሴሚናሪ የዐረብኛ ቋንቋ ለአንድ ዓመት ተከታትለዋል ።

አባ መዝገበ ሥላሴ ክፍሌ ምንም እንኳ ብዙ ጊዜ በትምህርት ላይ ቢሆኑ ባላቸው ጊዜ ሁሉ ለቤተክርስቲያን አገልግሎታቸውን አበርክተዋል በደብረ ሊባኖስ ገዳም በነበሩበት ጊዜ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ በገዳሙ ተግባር ቤት ያገለግሉ ነበር ።

አባ መዝገበ ሥላሴ ቀደም ሲል በ፲፱፻፶፮ ዓ/ም በደብረ ሊባኖስ ገዳም ሥርዓተ ምንኩስናን ከተቀበሉ በኋላ በዓመቱ በአዲስ አበባ በመንበረ ፓትርያርክ በቅድስተ ቅዱሳንማርያም ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅስናን ተቀብለዋል ።

አባ መዝገበ ሥላሴ ባላቸው ትምህርትና ፣ ባገኙት ማዕርገ ክህነት ቤተ ክርስቲያንን በይበልጥ ለማገል ገል።ይችሉ ዘንድ በሐረር ክፍለ ሀገር የቁልቢ ገዳም አስተዳዳሪ እንዲሆኑ ተሾመ ው ገዳሙን ለሁለት ዓመት በአስተዳዳሪነት መርተዋል ። ኢየሩሳሌም በሚገኘው የኢትዮጵያ ገዳም በነበሩበትም ወቅት ቤተ ክርስቲያንን ከማገልገላቸው ሌላ በገዳሙ ውስጥ ትምህርት ቤት አቋቁመው በኢየሩሳሌም የተወለዱትን ኢትዮጵያውያን ሕጻናት በመሰብሰብ አማርኛ ማንበብና መጻፍ እንዲያውቁ አድርገዋል ። በተጨማሪም በዚሁ ገዳም በነበሩበት ጊዜ ግዕዝና አማርኛ ለመማር የሚፈልጉትን የውጭ ዜጎች አስተምረዋቸዋል ። የኢትዮጵያውያን መነኮሳትም ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ በማሰብ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የእንግሊዝኛ ቋንቋና ሒሳብ አስተምረዋል ።

በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳሞች ራሳቸውን እንዲችሉ በማሰብ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ያበረከቱ የነበሩ ትጉህ ሠራተኛ አባት ናቸው ።



አባ ዜና ገብርኤል በጐ ሰው

# አባ ዜና ገብርኤል በጎ ሰው ፤

አባ ዜና ገብርኤል በጎ ሰው በጎንደር ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ በ፲፱፻፴፫ ዓ / ም ተወለዱ ። እድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ ሹምጌ በምትባል ደብር የቤተ ክርስቲያንን መሠረተ ትምህርት ከተማሩ በኋላ ቅኔ ከነአገባቡ ከመምህር ወልደ ነጕድጓድ ዘንድ ተምረዋል ። ወደ ሸዋ ክፍለ ሀገር መጥተው በደብረ ሊባኖስ ገዳም ቅዳሴ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ። በዚሁ ገዳም የሐዲሳትን ትርጓሜከመምህር ብርሃኑ ወ/ሥላሴ ዘንድ ተምረዋል ። እንዲሁም የአንደኛንና የሁለተኛን ደረጃ ትምህርታቸውን አዲስ አበባ በስዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት ተምረዋል ።

አባ ዜና ገብርኤል በጎ ሰው ከዚህም ሌላ ወደ ግሪክ አገር ተልከው በደሴተ ፍጥሞ በሚገኘው የመነኮሳት ማሰልጠኛ ሴሚናሪ ለሁለት ዓመት ከፍተኛ የቲኦሎጂ ትምህርት ተከታትለው በዲፕሎማ ተመርቀዋል ። በአቴና ዩኒበርሲቲ ደግሞ ለአራት ዓመታት የቲኦሎጂ ትምህርታቸውን ተምረው የባችለር ዲግሪ አግኝተዋል ።

አባ ዜና ገብርኤል በጎ ሰው በ፲፱፻፷፪ ዓ/ም በዝቋላ ገዳም የምንኵስናና የቅስና ማዕርግ ከመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ተቀብለዋል ።

አባ ዜና ገብርኤል በደብረ ሊባኖስ ገዳም ለሰባት ዓመት በእናኩዕነት ሠርተዋል ። በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በነበሩበትም ጊዜ ወጣቶችን የቅዳሴ ተሰጥዎ በማስተማርና እንዲሁም በአውሮፓውያን የሙዚቃ ምልክት እንዲቀናበር ረድተዋል ።

ከዚህም ሌላ አባ ዜና ገብርኤል በሐረር አደሬ ጢቆ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ፣ የሠሩ ሲሆን በቁልቢ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በግብዝና አገልግለዋል ። እንዲሁም ለእጲስቆጶስነት እስኪተጠሩ ድረስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት መንፈሳዊ ግልጋሎታቸውን ሲያበረክቱ ቆይተዋል ።



# አባ ዘሊባኖስ ፈንታ

አባ ዘሊባኖስ ፋንታ በጎንደር ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ በአለታ ወረዳ ልዩ ስሟ አረጊት ኪዳነ ምሕረት በተባለችው ገዳም በ፲፱፻፴ ዓ/ም ከብላታ ፈንታ ተሰማና ከወይዘሮ ለምለም ገሰሰ ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ በተወለዱበት ገዳም መሪጌታ ላቀው ከሚባሉ መምህር ንባብና ዳዊት ተማሩ ከዚያም በኋላ አጭታን ኪዳነ ምሕረት በምትባለው ደብር ምዕራፍና ጾመ ድጓ ተምረዋል ። ትምህርታቸውን ለመቀጠል ወደ ጎጃም ክፍለ ሀገር ሄደው ጎንጅ ቴዎድሮስ በተባለው ገዳም ቅኔ ለሁለት ዓመት ከመሪጌታ ወርቁ ተምረው ከ ተ ቀ ኙ በ ኋ ላ ወደ ዋሸራ በመዛወር በቅኔ ዝነኛ ከነበሩት ከመሪጌታ ማዕበል ፈንቴ ለሁለት ዓመት የቅኔ ትምህርታቸውን ተምረውአጠናቀዋል ከዚያም በኋላ ወደ ትውልድ ሀገራቸው ተመልሰው ምዕራፍ ጾመ ድጓና ድጓ ከመሪጌታ ሙጩ በደብረ ታቦር አውራጃ ልዩ ስሟ አጊዋ ጼዋን በተባለች ደብር የድጓ ትምህርት አጠናቀዋል ።

እንደገና ወደ አቋቋም ቤት በመግባት ለሁለት ዓመት መንጉዘር በሚባለው ደብር ከመሪጌታ ሚናስ የአቋቋም ትምህርት ተምረው ቁት አቡነ አረጋዊ በተባለው ደብር ከመሪጌታ ውብ አገኝ ለአንድ ዓመት ዝማሬ መዋስዕት ተምረዋል ከ ዚ ያ ም ወደ ደብረ ታቦር አውራጃ ተመልሰው ከጥንቱ መምህራቸው ከመሪጌታ ሙጩ ላቀ ዘንድ የድጓ ትምህርታቸውን በመቀጠል ጽፈውና አመልክተው ከጨረሱ በኋላ በ ነ ፋ ስ መውጫ አውራጃ በታች ጋይንት ወረዳ በምትገኘው በስመ ጥሩዋ በቤተ ልሔም አራት ዓመት ቆይተው ድጓ አስመስክረው በመምህርነት ተመርቀዋል ።

የድጓ ትምህርታቸውን ካስመሰከሩ በኋላ ወደተወለዱበት ገዳም ሔደው በአረጊት ኪዳነ ምሕረት ገዳም ለሰባት ዓመት ያህል ድጓ አስተምረዋል ።

አባ ዘሊባኖስ ቤተ ክርስቲያንን በብሕትውና ለማገልገል ስለፈለጉ ወደ ጎጃም ክፍለ ሀገር እንደገና ተመልሰው ጣና ገዳም በመግባት ሥርዓተ ምንኵስናን ከመምህር ኃይለ ማርያም ከተቀበሉ በኋላ ማዕርገ ቅስናን ከጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ ተቀብለዋል ።



አባ ዘሊባኖስ ፈንታ

የገዳምን ስነ ሥርዓት በይበልጥ ለማጥናት ስለፈለጉ በባሕር ዳር አውራጃ ልዩ ስሙ ጋሾላ በተባለ ገዳም ገብተው የገዳሙን ስነ ሥርዓት እያጠኑ ለሁለት ዓመት ገዳሙን ረድተዋል ። በገዳሙ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ እንጨት በመስበርና በመሸከም ውሀ በመቅዳትና ለእንግዶች ማረፊያ ቤት በመሥራት ገዳሙን አገልግለዋል ።

ከዚህ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ገዳም በቅዳሴና በማህሌት ከማገልገላቸውም በላይ ባላቸው ትርፍ ሰዓት በመጠቀም ትርጓሜ ሐዲሳትና አቡሻሕር እንዲሁም ዘመናዊ ትምህርት በመከታተል እስከ ዘጠነኛ ክፍል ተምረዋል ። በተጨማሪም በገዳሙ ውስጥ ለሁለት ዓመት በተከታታይ ተደርጎ በነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ኮርስ ተካፋይ ሆነዋል ።

የደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሆነው ከተሾሙ በኋላም በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የነበረውን ችግር ተገንዝበው ለቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች መኖሪያ ቤት አሠርተውላቸዋል ። እንዲሁም የእሑድ ትምህርት ቤት ወጣቶችም የመሰብሰቢያ አዳራሽ ስለአልነበራቸው አንድ አዳራሽ ከነሙሉ ድርጅቱ አሠርተው ሰጥተዋቸው ወጣቶቹ የነበረባቸውን ችግር አቃለውላቸዋል ። ተጀምሮ የነበረውንም የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ አሠርተው ሥራው ወደ መጠናቀቁ ደረጃ እንዲደርስ አድርገዋል ።

በደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ ምእመናኑን በሰበካ ጉባኤ በማደራጀት ከፍተኛ ሥራ ሠርተዋል ።

## አባ ያሬድ ግርማይ

አባ ያሬድ ግርማይ በትግራይ ክፍለ ሀገር በእንደርታ አውራጃ ጨለቆት ሥላሴ በሚባለው ቦታ በ፲፱፻፳፭ ዓ/ም ተወለዱ ። አባ ያሬድ ግርማይ ዕድሜያቸው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ ከአባታቸው ከቄስ ግርማይ ገብረ ኢየሱስ ፊደል ንባብና ዳዊት ካጠናቀቁ በኋላ ከመምህር ቀለመወርቅ ፀዋትወ ዜማን አጠናቀው ተምረዋል ።ቀጥሎም ከመምህር መንግሥቱ ኃ/ማርያም ቅዳሴ ዜማበሚገባ ተምረዋል። እንዲሁም ከፍተኛ ችሎታ የሚጠይቁትን የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች በልዩ ልዩ ትምህርት ቤቶች ከታወቁት ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዘንድ ተምረው በመምህርነት ደረጃ ተመርቀዋል ።

አባ ያሬድ የቅኔ ትምህርት በርከት ካሉ መምህራን ተምረው የቅኔ መምህር ናቸው። እንዲሁም የሐዲሳት ትርጓሜ ከታወቁት የሐዲስ መምህር ከአለቃ ሕሩይ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ፤ የመጻሕፍተ ሐዲሳት፣ትርጓሜ፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና አቡሻህር ፣ ከታወቁት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቅ ከመምህር ገ/እግዚአብሔር አጠናቀው ተምረዋል ። አባ ያሬድ የብሉያትን ትርጓሜ ከታወቁት ከአለቃ ጥሩነህ ፣ ካሣዬ ተምረዋል

አባ ያሬድ ግርማይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች የተራቀቁ የአራቱ ጉባኤያት ባለቤት ናቸው ።

አባ ያሬድ ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ያላቸው አባት ከመሆናቸውም በላይ ባላቸው ችሎታ ቤተ ክርስቲያንንና ኅብረተሰቡን በማገልገል አስተዋጽኦ አድርገዋል ። አባ ያሬድ ባላቸው ችሎታ ጉባኤ ዘርግተው ቅኔና የሐዲሳትን ትርጓሜ በማስተማር ብዙ ተማሪዎችን አስተምረዋል ።እንዲሁም በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ በነበሩበት ጊዜ ከመታሰቢያ ቤቱ ሊቃውንት ጋር የሰብከተ ወንጌልን ሥራ በመሥራት መጋቤ ሥርዓት ተብለዋል ። ከዚህም በስተቀር ወጣቶች የነገዩቱ ቤተ ክርስቲያን ደጋፊዎችና መሪዎች መሆናቸውን በመገንዘብ በበአታ ገዳም ውስጥ የመሠረተ ሃይማ





አባ ያሬድ ግርማይ

ኖት የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበርን በማደራጀት የግዕዝቋንቋንና የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን እምነት አስተምረው አሳውቀዋቸዋል ። በመታሰቢያ ቤቱ ባለው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሁለት ሺ በላይ የሚሆኑ ወጣቶችን የግብረ ገብ ትምህርት ከማስተማራቸውም በላይ ለት/ቤቱ ተማሪዎች መማሪያ የሚሆን በዘመናዊ መልክ የግዕዝ ቋንቋ ማስተማሪያ ጽሑፍ አዘጋጅተው ለመታሰቢያ ቤቱ ሰጥተዋል ።

አባ ያሬድ ግርማይ ከፍተኛ የሥነ ጽሑፍ ስሜትና ችሎታም ያላቸው ምሁር ናቸው ። በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ስም የተዘጋጀው ሥርወ ሃይማኖት የሚባለው መጽሐፍ እንዲታተም ሲዘጋጅ በማዘጋጀት አገልግለዋል ። የግዕዝም ሆነ የአማርኛ ፊደላት ያለቦታቸው እንዳይገቡ ማንም ሰው ሊጠቀምበት እንዲችል አድርገው በጽሑፍ አዘጋጅተዋል ።

የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት የራዲዮ መርሀ ግብር በነበረው ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በማዘጋጀት በራዲዮ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አስተምረዋል ።

አባ ያሬድ ግርማይወደ ትግራይ ተልከው በትግራይ ሀገረ ስብከት በየአውራጃውና ወረዳው ደከመኝ ወይም ሰለቸኝ ሳይሉ የሰበካ ጉባኤያትን አቋቁመዋል ። ከአቡነ ይስሐቅ ዲቁና ቅስናና፤ ምንኵስና በደብረ ሊባኖስ ተቀብለዋል ።

አባ ያሬድ ግርማይ ባላቸው የትምህርት ችሎታ የተደነቁ በሥራ ታታሪነታቸው ለሥራ ጓደኞቻቸው ምሳሌ የሆኑ በተማሪዎቻቸው ዘንድ የተወደዱና ፍጹም ትሁት አባት ናቸው ። እግዚአብሔርም ባወቀ ለበለጠ ሥራና ለዛሬዩቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጠርቷቸዋል ።

## አባ ተክለ ማርያም ዐሥራት

አባ ተክለማርያም ዐሥራት በትግራይ ክፍለ ሀገር በአጋሜ አውራጃ በስቡሕ ወረዳ በ፲፱፻፴፩ ዓ/ም ከአባታቸው ከአቶ ወልዱ ጊዮርጊስ ፣ ከእናታቸው ከወ/ሮ ከለላ ተወለዱ ።

ለትምህርት እንደደረሱም ቀሲስ ወልዱ ገሬማ ከሚባሉት ካህን ፊደልና ንባብ ተማሩ ። ከዚያም የኤርትራ ሊቀጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ ማዕርገ ዲቁና እንደተቀበሉ በዚያው ክፍለ ሀገር ተንቤን በሚባለው አውራጃ ውስጥ ጭኸ በሚባለው ታላቅ ገዳም በ፲፱፻፵፱ ዓ/ም በመግባት ገዳሙን ለ፲ ዓመታት እያገለገሉ ፤ ሰዓታትና ቅዳሴን ፤ አምስቱ አእማደ ምሥጢርንና ባሕረ ሀሣብን ፤ ከመምህር መንግሥተ አብ


ገብረ ማርያም ፤ ምዕራፍ ጾመ ድጓን ከመምህር ገ/ሥላሴ መዝገብ ቅዳሴን ከመምህር ተስፋ ማርያም ፈንታ ቅኔን ከመምህር ጌጡ ፅንቄ ባሕርይ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም የዚሁ ገዳም አበምኔት ከሆኑትና እንደወላጅ አባታቸው ሆነው ከሚ ጠሩባቸው ከመምህር ዐሥራት ጽዮን ማዕርገ ምንኩስናን ተቀበሉ ።

በዚሁ ዓመት ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የትግራይ ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ ማዕርገ ቅስና ተቀብለዋል ።

አባ ተክለማርያም ዐሥራት ሦስት ዓመት በሊቀ ረድዕነት ፤ አንድ ዓመት የገዳሙ ቄስ ገበዝ በመሆን ፤ እንዲሁም በገዳሙ ልዩ ልዩ ተግባሮች አገልግሎታቸውን አበር ክተዋል ከዚህም በኋላ በ፲፱፻፵፰ ዓ/ም አዞሱም ጽዮን ከሚገኙት ከመምህር ገብረ ጊዮርጊስ ጉባኤ ቤት በመግባት የአራቱን ወንጌላት ትርጓሜ ፤ ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ፤ ባሕረ ሀሳብ ፤ ከተማሩ በኋላ ወደጎንደር ክፍለ ሀገር በመዛወር ከዶ ክተር አባ አየለ ዓለሙ ጉባኤ ቤት በመግባት ፲፬ቱን የጳውሎስ መልእክታት ፤ የሐዋ ርያትን ሥራ ፤ የዮሐንስ ራዕይ ፤ ኪዳንንና ትምህርተ ኅቡዓትን ተምረው ካጠና ቀቁ በኋላ የሐዲስ መምህር በመሆን ተመርቀዋል ፤

ከዚህ በኋላ አባ ተክለማርያም ወደመነኮሱበት ገዳም ተመልሰው ሐዲስን በማ ስተማር ላይ እንዳሉ በ፲፱፻፷፬ ዓ/ም መጨረሻ ወደአዲስ አበባ በመምጣት በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በቅዳሴና በልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ተመ ድበው እየሠሩ ዘመናዊ ትምህርትን በመከታተል ላይ ሳሉ ፣ በ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሲመረጡ በጊዜያዊ ጉባኤ መራጭነት የፓ ትርያርኩ አቡነ ቀሲስና ም/ ልዩ ጸሐፊ በመሆን በማገልገል ላይ እንዳሉ ለዚህ ከፍተኛ ኤጲስቆጶስነት መመረጥ በቅተዋል ። አባተክለ ማርያም ዐሥራት ከብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ማዕርገ ቁምስናን ተቀብለዋል ።

አባ ተክለማርያም ዐሥራት




# አባ ፍሥሐ ጽዮን ጌታሁን


አባ ፍሥሓ ጽዮን ጌታሁን በ፲፱፻፲፯ ዓ/ም ከአባታቸው ከአቶ ጌታሁን ወልዱና ከእናታቸው ከወ/ሮ እርጎዬቀኝ በወሎ ክፍለ ሀገር በደብረ ዘመዶ ተወለዱ ። ዕድሜአ ቸው ለትምህርት እንደደረሰ በትውልድ ሀገራቸው ከመጋቢ ሽበሺ ንባብና ዳዊት ተማሩ ቀጥሎም ከመሪጌታ ኤልሳዕ ዜማ ከመምህር መልከ ጸድቄ (መልከጼዴቅ) ቅዳሴ ከተማሩ በኋላ ወደ በጌምድር ሄደው ቅኔ ፤ ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ትር ጓሜ ፤ ኪዳንና ትምህርተ ኅቡዓት አቡሻኽር ትርጓሜ ሐዲሳት ትርጓሜ ዳዊትና ትር ጓሜ ፍትሐ ነገሥት በመካነ ኢየሱስ ደብር ከታወቁት ሊቅ ከመምህር ገብረ ጊዮር ጊስ አጠናቅቀው ከተማሩ በኋላ በመምህርነት ተመርቀው የመምህራቸው ረዳት በመ ሆን ብዙ ጊዜ አስተምረዋል ፤ እንዲሁም ወደ ትውልድ ሀገራቸው ተመልሰው ለሰባት ዓመታት ያህል ወንበር ዘርግተው በማስተማር አያሌ ደቀመዛሙርትን አፍርተዋል ።

አባ ፍሥሐ ጽዮን ጌታሁን ባላቸው የመንፈሳዊ ትምህርት ፍላጎት ከላይ በተጠቀሰው የሙያ ዓይነት ብቻ ሳይወሰኑ እንደገና ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከታወቁት ምሁር ከመምህር ወልደ ማርያም ሲራክ ሰሎሞን ፤ መጽሐፈ መነኮሳት ማለት ማርይስሐቅ ፈል ክስዩስና አረጋዊ መንፈሳዊን ተምረዋል ፤ ከዚህም በስተቀር የጽሕፈትና የድጉስት ሥራ የተለየ እውቀታቸው ነው ።

አባ ፍሥሐ ጽዮን ጌታሁን የምንኩስና፤ የቅስናና የቁምስና መዕርግ የተቀበሉት የጎንደር ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ ሚካኤል ሲሆን በአገልግሎትም ረገድ ከ፲፱፻ ፷ ዓመተ ምሕረት ጀምሮበምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ቤት ክርስቲያን በማስተማር፤ ከ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ጀምሮ ከማስተማራቸው ጋር የዚሁ ደብር አስተዳዳሪ በመሆን መን ፈሳዊ አገልግሎታቸውን አበርክተዋል ።

አባ ፍሥሓ ጽዮን ጌታሁን





አባ ገብረ ሚካኤል መንገሻ

# አባ ገብረ ሚካኤል መንገሻ

አባ ገ/ ሚካልኤ መንገሻ በወሎ ክ/ሀገር በየጁ አውራጃ በሚገኘው በታላቁ ደብር በመርጦ ኢየሱስ በ፲፱፻፳፫ ዓ/ም ከአባታቸው ከአቶ ወ/ሚካኤል ወ/ኪዳንና ከእናታቸው ከወይዘሮ አማረች መንገሻ ተወለዱ ።

ዕድሜአቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ በተወለዱበት ደብር መሠረተ ትምህርትና ፀዋትወ ዜማ ተማሩ ። በተጨማሪም የቅዳሴ ትምህርት ተምረዋል የፀዋትወ ዜማን ትምህርት የተማሩት ከቀኝ ጌታ መንግሥቱ ቢያበይንና ከመሪጌታ ገ/ኢየሱስ እንዲሁም ከየኔታ ሐዋዝ ሲሆን ፤— የቅዳሴውን ትምህርት የተማሩት ደግሞ መምህር ወ/ መስቀል ከሚባሉ መንፈሳዊ አባት ነው ።

ከዚህ በኋላ የቅኔ ትምህርት ለመማር ወደ ዋድላ ደላንታ አውራጃ ማለት ዳውንት ውስጥ ሄደው ከመሪጌታ አድማሱ ቅኔ ፤ ተማሩ እንዲሁም በትውልድ ሀገራቸው በየጁ አውራጃ ግረም ጊዮርጊስ በሚባለው ቦታ ከመሪጌታ ሄኖክ እንደገና የቅኔ ትምሕርት ተምረዋል ። በተጨማሪም ወደላስታ አውራጃ ወደመቄት ሄደው ገረገራ ጊዮርስጊስ ከሚባለው ሥፍራ ከመምሕር ቀፀላ ሠይፈ ሥላሴ አሁን አቡነ እንድርያስ፤የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ ።

በዚያው ጥቂት ጊዜ ካስተማሩ በኋላ በ፲፱፻፵፮ ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ መንፈሳዊ ት/ቤት ገብተው ከመምህር ገ/ሕይወት ሠይፈሥላሴ የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜና የአቡሻህር (የቁጥር ትምህርት) ተማሩ ። እንዲሁም ጠቅላላውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ተከታትለዋል ።

አባ ገ/ሚካኤል መንገሻ በመንፈሳዊው አገልግሎት ረገድ በተማሩት ትምህርት ከ፲፱፻፵፰ —፲፱፻፶፬ ዓ/ም መሠረተ ትምህርትንና ትርጓሜ መጻሕፍትን በማስተማር ብዙ ደቀመዛሙርትን አፍርተዋል ።

ከ፲፱፻፶፬ —፲፱፻፷፭ በዚሁ በመታሰቢያ ቤቱ የመንፈሳዊና የዘመናዊ ትምህርት እንዲሁም የሰብከተ ወንጌል ኃላፊ በመሆን አገልግለዋል ። በዚሁ ጊዜ በት/ቤቱ የወላጆች ኮሚቴ ገንዘብ ያዥ በመሆን በእምነትና በጥንቃቄ እየሠሩ ኮሚቴውን በማስተባበር ፲ ክፍል ያለውን ት/ቤት አሠርተው በአገልግሎት ላይ ይገኛል ።



በ፲፱፻፷፭ ዓ/ም ወደሐረርጌ ክ/ሀገር በደብር አስተዳዳሪነት ተልከው የሐረር መካነ ሥላሴ ገዳም አስተዳዳሪ በመሆን ለ፫ ዓመት ያህል አስተዳድረዋል ። በአካባቢው የስብከተ ወንጌል ትምህርትን አስፋፍተዋል ። እንዲሁም ይኸው የተሾሙበት ቤተ ክርስቲያን በዘመን ብዛት ተጎሳቁሎ ስለነበር እንዲታደስ አድርገዋል ።

ለአብያተክርስቲያናት ለስብከተ ወንጌል የሚያስፈልጉትን መሣሪያዎች በማሟላትና ለአገልጋዮች ካህናት ደመወዝ በመመደብም ሆነ የኑሮ ሁኔታቸውን በማሻሻል ከፍተኛ የሥራ ድርሻ አበርክተዋል ። በ፲፱፻፷፰ ዓ/ም መጨረሻ ወደ አዲስ አበባ ተዛውረው የመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ በመሆን የሰበካ ጉባኤ በማቋቋም፤ሕዝበ ክርስቲያንን በማደራጀትና የካህናትን የኑሮ ደረጃ በማሻሻል ማለትም በ፳ ብር ደመወዝ የነበሩትን ካህናት ወደ ሰማንያ ብር ከፍ በማድረግ ታላቅ የሥራ ለውጥ አድርገዋል ።

አባ ገ/ሚካኤል በአገልግሎት ዘመናቸው ከሚያገለግሏቸው ወገኖችና ካገለገሉባቸው ሥፍራዎች ስለትምህርት ችሎታቸውና ስለ መልካም ጠባያቸው ልዩ ልዩ ሽልማቶች የምስክር ወረቀቶችን፤እንዲሁም ዲፕሎማዎችን ተቀብለዋል ። በዘመናዊም ትምህርት የ፩ኛ ደረጃን አጠናቀዋል ። አባ ገ/ሚካኤል መንገሻ ማዕርገ ምንኩስና የተቀበሉት በ፲፱፻፶፩ ዓ/ም ግንቦት ፲፪ ቀን በደብረሊባኖስ ገዳም ሲሆን የቅስና ማዕረግ ከአቡነ ማርቆስ በ፲፱፻፶፯ ዓ/ም ተቀብለዋል ። እንዲሁም የቁምስና ማዕርግ ከአቡነ እንድርያስ የተቀበሉ መሆናቸው ታውቋል ።

# አባ ስብሐት ለአብ በየነ

አባ ስብሐት ለአብ በየነ በጐጃም ክፍለ ሀገር በባህርዳር አውራጃ በቡሬ ወረዳ በ፲፱፻፳፩ ዓ/ም ከአባታቸው ከቀሲስ በየነና ከናታቸው ከወይዘሮ ዓለሚቱ ተወለዱ ። ለትምህርት እንደ ደረሱ የቤተ ክርስቲያኑን መሠረተ ትምህርት ፤ ከመሪጌታ ልሳነ ወርቅ ተማሩ ። እንዲሁም ከታወቁት መምህር ከመሪጌታ ብዙነህና ከመሪጌታ አየለ ፋንታሁን የቅዳሴን ዜማ ፥ በድጋሚ ተምረዋል ።



አባ ስብሐት ለአብ በየነ

የዲቁናን ማዕርግ ከጐጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ ተቀብለው ለብዙ ጊዜ አገልግለዋል ፤— ከዚህ በኋላም ወደ ተለያዩ አድባራትና ገዳማት በመዘዋወር የቅኔን ትምህርት ከነአገባቡ በመምህርነት ደረጃ ከአለቃ ዘቡሬ ፤ ከመሪጌታ ብዙአየሁና ከመምህር ጌበሬሉ አጠናቀው ተምረዋል ።

ከዚያም ወደ ጐንደር ክፍለ ሀገር በመሄድ በወገራ አውራጃ ከሚገኙት ከመሪጌታ ሥዩምና ከመሪጌታ አክሊለ በርሃን አቋቋም ከተማሩ በኋላ በየይትባሃላቸው የሚቆሙ ማኅሌቶችን ሁሉ በማዳመጥ የላይ ቤት የታች ቤት የማጋኢ ተብለው የሚጠሩትን ሁሉ አውቀው በመምህርነት እንደተመረቁ አቋቋም እያስተማሩ እንደገና በስቀልት ወረዳ በድጓ አስተማሪነት ከታወቁት ከመምህር መንክር ተሰማ በድጓ መምህርነት ተመረቁ አቋቋምንና ጾምትወ ዜማን አንድ ዓመት ከመንፈቅ ብዙ ደቀመዛሙርትን ሲያስተምሩ ከቆዩ በኋላ በገጠማቸው አንቅፋት ምክንያት ጉባኤውን በመፍታት ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም መጥተው በገዳሙ ከሚገኙት ከመምህር ብርሃኑ ወ/ሥላሴ የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ ፤ ከመምህ ፍሥሐ ክርስቶስ የትምህርተ ኀቡዓትንና ፣ የኪዳናትን ትርጓሜ ፤ እንዲሁም ባሕረ ሀሳብን ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ።

አባ ስብሐት ለአብ በ፲፱፻፳፮ ዓ/ም ወደ ወለጋ ክፍለ ሀገር ተዛውረው በነቀምቴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ፤ በመጽሐፍ ፤ በቅኔ ፣ በአቋቋም መምህርነት ተመድበው አዳሪ ተማሪዎችን በማስተማር ብዙ ደቀመዛሙርትን አስገኝተዋል ።

አባ ስብሐት ለአብ በዚሁ ክፍለ ሀገር በቅዳሴና በሰዓታት ፤ በማኅሌትና በስብከት በመሳሰሉት እንዲሁም በየገጠሩ በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት እየሄዱ ግዳጃቸውን በመፈጸም ስብከተወንጌልን በማስቀደም ሰበካ ጉባኤን በማቋቋም የወጣት መንፈሳዊ ማኅበርን በማጠናከር ተገቢ ትምህርት በመስጠት ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል ።

## አባ ሐዋዝ ብርሃኑ ።

አባ ሐዋዝ ብርሃኑ በሸዋ ክፍለ ሀገር በሰላሌ አውራጃ በኀሐ ጽዮን ወረዳ ኅዳር ፲፪ ቀን ፲፱፻፴፩ ዓ/ም ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት በደረሰም ጊዜ ፊደልና ዳዊት የንባብ አስተማሪ ከሆኑት ከአባ እንግዳ ተማሩ ። ከዚያም ጾምትወ ዜማን ከመምህር ዘገየ ፤ ቅኔን በመላ ኢትጵያ ከታወቁት ከመምህር ጥበቡ ጋሜ ተቀኝተዋል ።

በ፲፱፻፵፱ ዓ/ም ወደጎንደር ክፍለ ሀገር ሄደው በፋርጣና በጋይንት አውራጃ እየተዘዋወሩ ቁም ዜማ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ አቋቋም በደብረ ታቦር ኢየሱስ ከሚገኙት ከአለቃ ቀለመወርቅ ፤ እንዲሁም ከመርጌታ ወልደ ሰንበት ቀጽለው በ፲፱፻፶፯ ዓ/ም ወደ ጎንደር ርእሰ ከተማ በመግባት የጎንደርን ይትበሀል ላይ ቤትና ታችቤት አቋቋም በሚገባ አጥንተዋል ።

አባ ሐዋዝ ብርሃኑ በጎንደር ከተማ ብሉይ ከሚያስተምሩት ከመምህር ወልደሰንበት ብሉይ በመቀጸል ላይ ሳሉ መምህሩ ስለዐረፉ በወንበራቸው ከተተኩት ከመምህር ጸጋ ሲማሩ ከቆዩ በኋላ እንደገና ከመምህር ኃ/ማርያም ብሉያትን ተምረው አጠናቀዋል ።

አባ ሐዋዝ ብርሃኑ ትምህርታቸውን በመቀጠል ሐዲሳትን ከመምህር ክፍሌ እየቀጸሉ በትርፍ ጊዜያቸው ለደቀመዛሙርቱ እያስተማሩ በተጨማሪም ለከተማው ምእመናን ወንጌልን በመስበክ አገልግለዋል።ይልቁንም መጽሐፈ ሊቅ ከዶክተር አባ አየለ ሲቀጽሉ ከቆዩ በኋላ መማር ለማስተማር መሆኑን በመገንዘብ በጐንደር በየአውራጃውና





አባ ሐዋዝ ብርሃኑ

በየወረዳው እየተዘዋወሩ ወንጌልን አስተምረዋል። ከዚያም በ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ወደጉባኤ ቤት ተመልሰው በማስተማር ላይ እንዳሉ በክፍለ ሀገሩ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ እንድርያስ ትእዛዝ ሐዋርያዊ ተልእኳቸውን እንዲፈጽሙ ስለተደረገ በስብከተ ወንጌል ሥራ እስከ ተከዜ ወንዝ አካባቢ በመሄድ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ምእመናንን በማስተማርና በማስተባበር የሰበካ ጉባኤ አቋቁመዋል ።

ከዚህ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ከተማ መጥተው በኮርስ ላይ እንዳሉ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ እዚሁ እንዲቆዩ ተደርጎ በአዲስ አበባ አድባራት እየተዘዋወሩ በማስተማር ላይ ሳሉ የገነተ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ በመሆን ተሾሙ ። ከዚያም በቅዱስ ፓትርያርኩ ፈቃድ የደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሆነው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል ላይ እንዳሉ ለኤጲስቆጶስነት መመረጥ በቅተዋል ።

አባ ሐዋዝ ብርሃኑ በ፲፱፻፵፯ ዓ/ም ክብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የዲቁና ማዕርግ ፣ በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም በማኅበረ ሥላሴ ገዳም የምንኩስና ማዕረግ ፤ በ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ የጎጃም ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ የቅስና ማዕርግ ተቀብለዋል ።

## አባ ኅሩይ ወልደ ሰንበት

አባ ኅሩይ ወልደ ሰንበት በ፲፱፻፵ ዓ/ም በጐንደር ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ በመካነ ሰማዕት ገላውዴዎስ ከአባታቸው ከአቶ ፈንታ ወልድየና ከእናታቸው ከወ/ሮ ወለተ ተክለ ሃይማኖት ተወለዱ ። ዕድሜአቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ በተወለዱበት ደብር በመካነ ሰማዕት ገላውዴዎስ የድጓ መምህር ከነበሩት ከመምህር ሙሉጌታ ኃይሉ የቃል ትምህርትና ጾመድጓ ተምረዋል ። ከዚያም ወደ ሸዋ ክፍለ ሀገር መጥተው በደብረ ብርሃን አውራጃ በናስ ማርያም ከአለቃ ቤተ ማርያም ድጓ፤ በምግልዋሻ ገብርኤል ከአለቃ ኃይለ ጊዮርጊስ ቅኔ ተምረዋል።እንዲሁም ከልዩ ልዩ መምህራንና ከተለያዩ ቦታዎች አቋቋምና ቅኔ ተምረዋል ።



አባ ላዕከ ማርያም ማንደፍሮ

አባ ላእከ ዲቁናን የተቀበሉት ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ ሲሆን ምንኩስናና ቅስናን የተቀበሉት ከብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ነው ። ቁምስናን ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በ፲፱፻፶፩ ዓ/ም ተቀብለዋል ።

ከ፲፱፻፵፱ እስከ ፲፱፻፶ ዓ/ም በገበዩት ትምህርት እውቀት ጋሙጎፋ ክፍለ ሀገር የመጽሐፍ ቅዱስና የግብረ ገብ መምህር በመሆን ሠርተዋል ። ከ፲፱፻፶ እስከ ፲፱-፻፶፫ ዓ/ም የግብረ ገብ ፤ የእንግሊዝኛና የአማርኛ ቋንቋዎች መምህር በመሆን በዓፄ ልብነ ድንግል ወናግ ሰገድ ት/ቤት ደብረ ዘይት አስተምረዋል ። በዚሁ ት/ቤት ለተማሪዎችና በአካባቢው ለሚገኘው ሕዝብ ጠቃሚ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስና ጠቅላላ የመንፈሳዊ ስብሰባ አቋቁመው ስለነበር በሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ሊማርበት ችሏል ።

ከ፲፱፻፶፫ እስከ ፲፱፻፶፩ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ሞግዚት በመሆን ሠርተዋል ።

ከ፲፱፻፶፯ ዓ/ም ጀምሮ እስከአሁን ድረስ በኒዮርክና በልዩ ልዩ ምዕራብ አገሮች ባሉት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በአስተዳዳሪነት ሠርተዋል ። ከዚህ በታች ስማቸው በተጠቀሱትም አገሮች ላይ አብያተ ክርስቲያናትን አቋቁመዋል ።

፩/ በኒውዮርክ ፪/ ካሊፎርኒያ ፫/ በካናዳ ፬/ በሎንዶን ፭/ በበርሙዳ ፮/ በጃማይካ ዌስት እንዲስ በተጨማሪም በአንቲጋ ሴንት ክርስቶፎር ዶሚኒካ ጆርጅያ በተባሉት አገሮች ቤተ ጸሎቶችን አቋቁመዋል ። በተለይ የጃማይካ ቤተ ክርስቲያን ፱ ቅርንጫፎች ያሉት ሲሆን ፰ሺ (ስምንት ሺህ) ምእመናን አጥምቀዋል። ለምእመናንና ለካህናት ማሰልጠኛ የሚሆን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ርዳታ በመጠየቅ የትምህርት ቤት አሰርተዋል ። ይኸውም ት/ቤት የአማርኛ ቋንቋ የኢትዮጵያ ባሕልና ጠቅላላ የአፍሪ



ካ ታሪክ ይሰጥበታል ። በተጨማሪም የዳቦ ቤትና ልዩ ልዩ የተግባረ ዕድ ሥራዎችን አቋቁመዋል ሥራ የሌላቸው ምእመናን በዚሁ ቦታ እየሠሩ ለመኖር ችለዋል ። የጃማይካ ቤተ ክርስቲያን ለሕዝብ በሚያደርገው ጠቃሚ ሥራ ስለታወቀ በጃማይካ ካውንስል ኦፍ ቸርችስና በካረቢያን ኮንፈራንስ ኦፍ ቸርችስ ቀዋሚ አባል ሆኖአል ። በተለይም ባለፈው ወር የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ በዚሁ አገር ተደርጎ ስለነበር የገናን በዓል ጸሎት እንድናዘጋጅ ተጠይቆ በቤተ ክርስቲያናችን ስነ ሥርዓት ተዘጋጅቶ አ ሥ ር የሚሆኑ ጳጳሳትና በመቶ የሚቆጠሩ የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞች በተገኙበት ሥርዓተ ጸሎቱ በሚገባ ተከብሮ ውሎአል ። በዚሁም ምክንያት የተነሣ የጃማይካ ቤተ ክርስቲያን ራስዋን ችላ በማዕከላዊ የአብያተ ክርስቲያናት ስብሰባ ተካፋይ እንድትሆን ስለተፈቀደና ጥሪ ስለደረሰችው በተመልካችነት የስብሰባው ተካፋይ ሆነው ነበር ። ይኸውም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅርንጫፍ ራስዋን ችላ በእንዲህ ያለ ስብሰባ ስትሳተፍ በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ ነው ።

በምዕራብ አገሮች ያሉት አብያተ ክርስቲያኖቻችን የሚገኙት በተራራቀ ቦታ ስለሆነ ከእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ቅርንጫፍ መልእክተኞች እየተገኙ ስለ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ዕድገትም ሆነ መሻሻል የሚወያዩበትን ስብሰባ አቋቁመዋል።ስብሰባውም በጣም ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል። በነዚሁ አብተ ክርስቲያናት በጠቅላላው ፲፱ሺ፩፻ ምእመናንን አጥምቀዋል ።

በስነ ጽሑፍ፤ በኩልም አንድ አጭር የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክና ዕምነት አንድ የ ጋብቻ ሥነ ሥርዓት በእንግሊዝኛ ቋንቋ አሳትመው ለምእመናኑ አበርክተዋል ። ሦስተኛውም መጽሐፍ በማተሚያ ቤት ይገኛል ።

በዩጎዝላቪያ ፕራሃ ላይ ተደርጎ በነበረው የዓለም ሰላም ስብሰባና በመስኮብ አገር በጃማይካ የነጻነት በዓል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኛ በመሆን ተካፋይ ሆነዋል ።